# አቤቱታ ከኢትዮጵያ።

ደራሲ፤ ስምሰም ፀጋው

መስከረም 1, 1992 ዓ.ም.

## መግቢያ

አንድ ወዬ ባይ ሙሾ ሲያወርዱ እንዲህ አሉ፦
«ለቆመ አልቅሱ ምን ለሞተ ብቻ፤
ሥርተን ለግብር ነው ወልደን ለዘመቻ።
እውኝ...አለ ጅቡ አወይ መከራዬ፤
እግሬን ሊጉትተኝ ከበስተኃላዬ፤
መለሰ ብለህ ያዘው እባክህ ጌታዬ።»

የሚቀጥለው ግጥም በዚህ ወዬታ/እሮሮ የተነሣሣ ቢሆንም፤ በደቡብ፣ በመሐልና፣ በሰሜን ኢትዮጵያ ያለውን የተራ ሕዝብ እሮሮ ያንፀባርቃል።

# አቤቱታ ከኢትዮጵያ።

አቤት! አቤት! አቤት!
አርማችን ሆነ ወይ፣
እርሃብና እልቂት!
አቤቱታ ላቅርብ ለራበው ወንድሜ፣
አቤቱታ ላቅርብ ለራባት እህቴ፣
አቤቱታ ላቅርብ ለራበው አባቴ፣
እንጀራ ብትሰጠኝ
ያች ኢትዮጵያ እናቴ።
አልቃሾቹ ጮሁ በደቡብ በሰሜን፣
ተሸክሜ እንድንዝ አቤቱታቸውን።
እሮሮረዋቸው ይህ ነው ለሚሰማ አዛውንት፣
አርማችን ሆነ ውይ እርሃብና እልቂት።
«ለቆመ አልቅሱ ምን ለሞተ ብቻ፣
ሥርተን ለግብር ነው ወልደን ለዘመቻ።
እውኝ አለ ጅቡ አወይ መከራዬን
እግሬን ሊጉትተኝ ከበስተኃላዬ፤
መለሰ ብለህ ያዘው እባክህ ጌታዬ።»
ዘመድ ለመጠየቅ አገር ቤት ወርጄ፣
ውዶ አሞራ ገደል አልፎ ደብረ ታቦር፣
ጉጡ ሸንተረሩ መሰለኝ መቃብር።
እርቅናው ቢመታኝ በግራና በቀኝ፣
ውዶ አሞራ ገደል እንግዳ ሆነብኝ።
ወይ ቸሩ ጠንበሎ ፍርሃቴን ሊሸፍን፣
ዓይኔን አስጨፍኖ አስተኛኝ እንቅልፌን።
ፎግራ፤ አዲስ ዘመን በሕልሜ እንዲህ አለኝ፣
አይዞሽ አትደንግጭ ይልቅስ ታዘቢ መዝግቢ፣
ዘመኑ ካመጣሽ፣
አዳምጭ ቀጥ ብለሽ፣
እውነቱን ላስረዳሽ፣

አዳምጠኝ መቀሌ ሌላው ይቅርና፣
ደማቸው አትሟል እንፋረድ ብሎ፣
ይኸ ቀን ያልፍና፤
አዳምጠኝ ወልቃይት ሌላው ይቅርና።
ልንገርህ አድዋ፣
አዋጁ ታውጇል፣
ላስተማሪ ጭምር፤
መምህርናን ትቶ፣
እንዲሆን ወታደር።
ለማስተማርማ አሉ ቅዱስ ጳውሎስ
ሥድስት ኪሎ ገብተው፣
ቅድስተ ቅድሳን፤
ለነፍስ ብቻ ሳይሆን፤
ክልሉ እንዲፀድቅ
ሊማጠኑ አሳዛን።
አቤት! አቤት! አቤት!
ሥማኝ ወዶ ገነት፣
አዲሱ መዋቅር ጨርሰ ወይ እንጨት፤
ለማገዶ አዘዘ አፈርና ኩበት።
አቤት! አቤት!
ግዞት ያስሄዳል ወይ፣
በኢትዮጵያ እምነት፣
እባክህ አስረዳኝ የምትኖረው ነቀምት፣
ምነው በተገኘሽ እትዬ ጣይቱ፤
ዛሬም እንደገና
ድንበር ሲያሟግቱ።
ይህን አቤቱታ እናንተ አዳምጡት፣
ዛሬ ሸንጎ ናቸሁ ነገ ቤተ-መንግስት።
ጣጣ አታምጡብኝ፣
ሌላም ዘር አትጫኑኝ፣
ቀለሜ ቢጠቁርም፣
በክልል መታቆር
ጭራሽ ጭራሽ አልፈልግም።
አገሬ ኢትዮጵያ ጉጤ በጌምድር፤
በፍጹም አልፈቅድም በክልል መታቆር፤
መብቱ የኔ ነው ከፈለግሁት መኖር።

አዳምጠኝ መቀሌ ሌላው ይቅርና፣
ደማቸው አትሟል እንፋረድ ብሎ፣
ይኸ ቀን ያልፍና፤
አዳምጠኝ ወልቃይት ሌላው ይቅርና።
ልንገርህ አድዋ፣
አዋጁ ታውጇል፣
ሳስተማሪ ጭምር፤
መምህርናን ትቶ፣
እንዲሆን ወታደር።
ለማስተማርማ አሉ ቅዱስ ጳውሎስ
ሥድስት ኪሎ ገብተው፣
ቅድስተ ቅድሳን፤
ለነፍስ ብቻ ሳይሆን፤
ክልሉ እንዲፀድቅ
ሊማጠኑ አሳህን።
አቤት! አቤት! አቤት!
ሥማኝ ወዶ ገነት፣
አዲሱ መዋቅር ጨርሰ ወይ እንጨት፤
ለማገዶ አዘዘ አፈርና ኩበት።
አቤት! አቤት!
ግዞት ያስሄዳል ወይ፣
በኢትዮጵያ እምነት፣
እባክህ አስረዳኝ የምትኖረው ነቀምት፣
ምነው በተገኘሽ አትዬ ጣይቱ፤
ዛሬም እንደገና
ድንበር ሲያሟግቱ።
ይህን አቤቱታ እናንተ አዳምጡት፣
ዛሬ ሸንጐ ናቸሁ ነገ ቤተ-መንግስት።
ጣጣ አታምጡብኝ፣
ሌላም ዘር አትጫኑኝ፣
ቀለሜ ቢጠቁርም፣
በክልል መታቆር
ጭራሽ ጭራሽ አልፈልግም።
አገሬ ኢትዮጵያ ጉጤ በጌምድር፤
በፍጹም አልፈቅድም በክልል መታቆር፤
መብቱ የኔ ነው ከፈለግሁትት መኖር።
ለዚህ አቤቱታ እስኪ ጆሮ ስጡት፣
እኔ ታዛቢ ነኝ ተራ ሕዝብ ባለቤት፣
እንባ አስጠባቂዋ፣
የኢትዮጵያ ልጅ እያልሁ ነው አቤት።
ጥያቄ ልሠንዝር በጥሞና አስቡት፣
ችሎት ላይ ስትሆኑ
ምን ትፈርዱ ይሆን፣
ለኢትዮጵያ እምነት?

ፎግሬ፤ አዲስ ዘመን በሕልሜ እንዲህ አለኝ፣
አይዞሽ አትደንግጭ ይልቅስ ታዘቢ መዝግቢ፣
ዘመኑ ካመጣሽ፣
አዳምጭ ቀጥ ብለሽ፣
እውነቱን ሳስረዳሽ፣
በወረቀት ጣፊው በሞቴ እባክሽ።
በእውነት አይን እይው ጋራ ሸንተረሩን፣
መፍረድ አይቀርም ጊዜ የመጣ ለት፣
አጥንት ደም ፈሷል ለኢትዮጵያዊነት፣
    በይ ስሚ አዳምጭኝ ልንገርሽ በእውነት፣
    እርማችን አይደለም እርሃብና እልቂት።
ሂጅ ተናገሪ አደራ የኔ ልጅ፣
መዋረድ አይሆንም መባል ኢትዮጵያዊት፣
ያያምቶችሽ ደም ነው የሰጠሽ ነፃነት።
    አተኩረሽ እይው ዘንግ ተራራውን፣
    ቅጠሉን ቢያሆጩም፣
    መንፈስ ያዘለውን።
እውንት ነው መዝግቢ ይሆን አቤቱታ፣
ከጉዳት ላይ ጉዳት ከበደል ላይ በደል፣
በክልል ተገርፋል ውዶ አሞራ ገደል።
ጋራው ሸንተረሩ የሚጣራው ከሩቅ፣
ጉንደር ፋሲለደስ አለፍ ብሎ ደባርቅ፣
መንፈሱ አምጿል ዛላው እንኳን ቢደርቅ።
አዝመራው ተግዟል እንኳንስ ከብቶቹ፣
ዛሩ እንኳን ተግዟል እንኳንስ ልጆቹ፣
ጣናም ዘመተ አሉ በጋይንት ኤርትራ፣
ዘመድ ለመጠየቅ ሊካፈል መከራ።
    በሰሜን፣ በደቡብ፣ በመሐል ገፈርሳ፣
    ከየቱ ጀምሬ የትኛውን ላውሳ።
ሸህ ቀሳውስት ሳይላይ፣
ነጋዴ ገበሬ እፁብ ነው ትይንቱ፣
እርቃናቸው ጡፏል ሕፃን አዛውንቱ።
    አዳምጠኝ አዲግራት ሌላው ይቅርና፣
    መዝግብ ስማቸውን የኢትዮጵያን ልጆች፣
    ደማቸው ቀለም ነው ፊታቸው ብራና፣
    ቸለል እንዳተለው አደራ በጠና።
ሁሉንም ለታሪክ መተው እንፈልግም፣
እንፋረዳለን ይኸ ቀን ያልፍና፣
ወልቃይት አዳምጠኝ ሌላው ይቅርና።
    ቅን ፈራጅ ለችሎት መቀመጡ አይቀርም፣
    ይዘት ተለውጦ ዘመኑ ቢረዝምም።
ኡኡ ለማን ልንገር ፈራጅ እስኪመጣ፣
ልሃድ ወደ ወሎ ልንገር ላላማጣ፣